# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 37

ጥቅምት 20 ቀን 2015 ዓም(30-10-2022)

የዛሬውም ጥንቅራችን እንደሌሎቹ ሳምንታት በአገራችን በኢትዮጵያ የተከሰቱትን አበይት ጉዳዮች አንስተን የምንተችበት ይሆናል።በአገራችን የሚከሰቱት ሁሉም በሚባል ደረጃ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተቶች በመሆናቸው ያንን የሚመለከት በመሆኑ መልካም ነገር እዬተሰማና እዬታዬ ሆን ተብሎ መጥፎ መጥፎውን ብቻ እዬመረጥን ትኩረት የምንሰጥ አለመሆኑን አድማጮቻችን ያውቁታል ብለን እንተማመናለን።

በመሬት ላይ ያለውን ብዙውን መጥፎ ነገር ከዶና ዘንግቶ ሕዝብ ሲራብ ጠገበ፣ምርት ተትረፍርፎ ከራሱ አልፎ ለሌሎቹ ተረፈ፣ሲፈናቀልና ቤቱ ሲፈርስ ቤት ታደለ፣ሲጨፈጨፍ መንግሥት ለህይወቱ ዘብ ቆመለት---ወዘተ የሚሉ የሃሰት ፈጠራዎች የመንግሥትን አስከፊና እውነተኛ ገጽ ለመሸፈን የሚዘግቡ ብዙዎች እንዳሉ የሚካድ አይደለም።የሕዝቡን እውነተኛ ኑሮና ሰቆቃ ለመዘገብ የደፈሩት ሃቀኞች ለእስራትና ለወከባ ሲዳረጉ እያዬ ለእውነት የሚቆመው በጣም ጥቂቱ ሆኗል።ደግነቱ እኛና እኛን የመሳሰሉ ደፋሮችና አገር ወዳዶች የመናገርና የመጻፍ ነጻነት በሚከበርበት አገር ውስጥ መሆናችን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ ብንሆን ኖሮ በእስርቤት ውስጥ ከሚማቅቁት ጎን አብረን በተሰቃዬን አለያም በአፋኝና ገዳዮች እጅ ደማችን ፈሶ በቀረ ነበር።

በዚህ ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ እንደሌሎቹ ሳምንታት ሁሉ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ይበልጥ እያሽቆለቆለ የሄደበት ፣ያገሪቱ ገንዘብ ተመኑን ያጣበት፣የጥቁር ገበያ የናረበት፣የንጹሃን ደም ከመፍሰስ ያላባራበት፣ መፈናቀል የዕለት ተግባርና ግዴታ የሆነበት፣የጎሳ ማንነት ወሳኝና የመኖር ወይም ያለመኖር ዕጣፈንታ የሚወሰንበት መሆኑ ይበልጥ ተጠናክሮ የታዬበት ሳምንት ነው።በክፍላተሃገር ብቻ ሳይሆን በዋናዋ ከተማ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚፈጸመው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆነ የቡድን ወንጀል ይበልጥ እያደገና እዬተስፋፋ ሄዷል።ሕጻናት ሳይቀሩ የመደፈር፣የመገደልና ታፍኖ የመወሰድና ሕይወታቸው በገንዘብ የሚደራደሩበት የጭካኔ ባህል ሰፍኗል።በአጠቃላይ የሰው ልጅ ህይወት ከዶሮ ህይወት የረከሰ ሆኗል። ለሕዝብ ያልቆመ ወንጀለኛ መንግሥት ባለበት አገር ውስጥ ከዚህ የተለዬ ሰላማዊና ፍትሃዊ ሥርዓት አይኖርም። ተመልከት አለቃህን እንዲሉ የመንግሥት ተግባር ለተከታዩ ፋና ወጊ ነው።

መንግሥት ተብዬው ተረኛ የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ቡድን ካለማንም ጠያቂና ተቃውሞ ያሻውን ማድረጉን ቀጥሎበታል።ብዙ የከተማዋ ነዋሪዎች ለኦነግ መሪ ቤተመንግሥት መሥሪያ ሲባል ከኖሩበት ቦታ ተፈናቅለው ሜዳ ላይ ፈሰዋል።የፍትሕ ያለህ ብለው ቢጮሁም ሰሚ አላገኙም።ተሰብስበው ለአቤቱታ በዬሄዱበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚጠብቃቸው የፖሊስ ቆመጥ ነው።ጥያቄያቸውን መስማት ቀርቶ ከመሥሪያ ቤቱ ግቢ እንዳይገቡ በጥብቅ የተከለከለ ነው።ኢትዮጵያውያኑ ለመግባት በሚከለከሉበት ግቢና ቢሮ ውስጥ አሸቃባጮችና የውጭ አገር ባለሃብቶች ታጅበው ይርመሰመሱበታል።ወርቅ የተጫነች አህያ የማታልፈው የግምብ አጥር የለም የሚባለው በገሃድ የሚታይባት አገር ሆናለች። ወንጀለኛው ሥርዓት የፈለፈላቸው ወንጀለኞች በሕዝቡ ላይ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆነውበታል። በሰላም ወጥቶ ለመግባት የጸሎት ሁሉ መጀመሪያ ሆኗል። ኑሮ በዚህ ቢለው በዚያ ዙሪያው ገደል ሆኖበታል።አቤት የሚልበት የፍትሕ ተቋምና ሕግ አስከባሪ የለውም።ው

ለስሙ ዜጋ ይባላል እንጂ የዜግነት መብቱ ያልተከበረለት ማንም እንዳሻው የሚያድነው የሜዳ እንስሳ ሆኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ሕዝብ የከተማዋ ባለቤትነቱን ተነፍጎ የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ለተባለ ባለጌና ዋልጌ ስብስብ ጭሰኛ እንዲሆን ተፈርዶበታል።ጭሰኛነቱንም ለኦሮሚያ ለተባለ ክልል ከገቢው እስከ 50% በዓመት ግብር እንዲከፍል አስገዳጅ ትዕዛዝ ተላልፎበታል።ይህንን ኢፍትሃዊ ድርጊት ለማወናበድ ሌሎች የክልል ከተሞች ለዬክልላቸው ተመሳሳይ ግብር እንዲከፍሉ ታዘዋል።በጣም የሚገርመው ሌሎቹ ከተማዎች እንዲከፍሉ የተጣለባቸው ግብር ላሉበት ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማን ለዬት የሚያደርገው ግን ለማትገኝበት የኦሮሞ ክልል ባለዕዳ መሆኗ ነው። ይህ የተንኮልና የማናለብኝ ሥራ የተጀመረው ዛሬ ሳይሆን ውሎ አድሯል።ይህ ለኦሮሞ ልዩ ጥቅም በሚል ሽፋን የተጀመረው ገፈፋ አሁን ተግባራዊ እንዲሆን ሕጋዊ ቅርጽ ይዟል።ኦሮሞ ያልሆነውን ኢትዮጵያዊ ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን በሆነ ባልሆነው መንገድ ንብረቱን በመዝረፍና በማስመረር ጥሎ እንዲወጣ የማድረጉ ሴራ ከፍ ብሎ የከተማዋን ዳርቻ እንደ ሽከላ እዬሸረፉ የሚሟቱ ድፍረት ታክሎበት ለቀጣዩ ከተማዋን ሙሉ ለሙሉ የመዋጥ ሂደት መንደርደሪያ ሆኗል።

ጥቂት የማይባሉ ግፍና በደሉ ያስመረራቸው ፤ቤታቸው ፈርሶና ቦታቸውን ተነጥቀው ሜዳ ላይ የፈሰሱ፤አዛውንቶች፤ሴቶችና ህጻናት የፍትህ ያለህ እያሉ ቢጮሁም ሰሚ አላገኙም።ይህንን ያስፈጸመችው የከተማዋ ከንቲባ በውጭ አገር ለጉብኝት ስትሽከረከርና በዬአዳራሹና በዬኤምባሲው ቢሮ ኬክ ስትቆርጥ ትውላለች።በቅርቡ በአሜሪካ በዋሽንግተን ከተማ ባለው ኤምባሲ ውስጥ የታዬው ትእይንት ምስክር ነው።በዚህ የማን አለብኝ ስሜት የታጀበ ስብሰባ ላይ ከታደሙት የሥርዓቱ አጃቢዎችና በወገኖቻቸው ጉዳትና መፈናቀል ለቦታ ቅርምትና ለልዩ ልዩ ጥቅም ከተሰለፉት መካከል አንዱ "የኔ ጀግና፤አንችን በማዬቴና ባንች ፊት በመቆሜ እንደገና ተወለድኩ፤ኩራትና ደስታ ይሰማኛል፤ ክፉ አይንካሽ፤ካንች በፊት ያስቀድመኝ" በሚል መልኩ ሲቀባጥር ስናዬው በአርቲስት ማዲንጎ የቀብር ስነ ስርዓት ላይ መድረኩን ይመራ ዬነበረው እኛ ወረደ ብለን የሰዬምነው ይህችኑ ከንቲባ ተብዬ "ጀግናዋ፤ቆራጧ!" ሲል በማወደስ የአትርሽኝ መልእክቱን ካሰማው ብርሃኑ ከተባለው አድርባይ ጋር የተወዳደረ ይመስላል። ለአድር ባዮቹ ጀግንነት ማለት ደሃውን ሕዝብ ማፈናቀል፤መዝረፍ፤ መግደል፤መሆኑን ተገንዝበናል።እንዲህ አይነቶቹ ይሉኝታ ቢስ ሆድ አደሮች ናቸው የአምባገነኖች ምርኩዝ ሆነው የሚያገለግሉት።

ሕዝቡ በተለይም የጉዳቱ ሰለባ የሆነው በነዚህ አይነቶቹ ላይ እርምጃ እንዲወስድ ብዙ ጊዜ ተናግረናል፤አሳስበናል።ግን ሕዝቡ አሁንም ከእንቅልፉ አልነቃም።ያም ስለሆነ የሥርዓቱ አወዳሽና አሽቃባጩ ሜዳውን ሞልቶታል።ሕዝቡ ስለመብቱና ስለአገሩ ሊኖር የሚገባው ግንዛቤ የደበዘዘ ይመስላል።ስለሱ የሚጮሁት በእስር ቤት ሲማቅቁ ለማስፈታት እርምጃ መውሰድ ቀርቶ ዞሮ ለማዬትና ለምን ብሎ ለመጠዬቅ አልደፈረም።አንዱ በሌላው ኪሳራ፤ጉዳትና መከራ መኖርን የመረጠ ይመስላል። ብሔራዊ የሚባል የጋራ ህሴት ፍርክስክሱ ወጥቷል።የብላ ተባላ ዘመን ሆኗል።ለዚያም ነው አንድነትና ድፍረት በሌለበት አገር የውስጥና የውጭ አጥፊ ሃይሎች ያሻቸውን ለማድረግ ዕድል የሚያገኙት።

ላለፉት ሁለት ዓመታት በሰሜኑ ያገራችን ክፍል ሲካሄድ የቆዬው ጦርነት መቋጫ አላገኘም።አሁንም ድረስ ደም መፋሰሱ ቀጥሏል።የመንግሥት ሃይል ጦርነቱን በበላይነት የሚመራ እንደሆነ ብዙ ቢነገርም ድል ለማድረግና ለመቋጨት አልቻለም።አለመቻልም ሳይሆን የሚፈልግ አይመስልም።

1 የሥርዓቱ ቁንጮ የሆነው ግለሰብ አብይ አህመድና የወያኔ መሪዎቹ ጦርነቱን የሥልጣን ገበጣ ጨዋታ አድርገው ስለሚጠቀሙበትና መጠናቀቁ ለሌላ ሕዝባዊ ጥያቄና ተቃውሞ ስለሚያጋልጣቸው ሕዝቡን ፋታ የመንሳትና ትኩረቱን የማስለወጫ ዘዴ አድርገው ስለሚጠቀሙበት፣

2 ሁለቱም ሃይሎች ጦርነቱን ለውጭ መጠቀሚያና መደራደሪያ ለማድረግ ስለሚሹ እንዲቆም አይፈልጉም ፣የታማኝነት ማሳያና መለኪያ አድርገው ይቆጥሩታል።

3 የወያኔ መራሹ ጦር የሚያገኘው የውጭ አገር እርዳታና የመሪዎቹ ፕሮፓጋንዳ ተብትቦ ስለያዘው እምቢ ቢል ያው ሞት ስለሚጠብቀው፣ እንዲሁም በጦር ሜዳ የሚዘርፈው ንብረት ስለሚያጓጓው መዋጋቱን የመረጠ ይመስላል።

3 ጦርነቱ እንዲቆምና ሰላም እንዲፈጠር አስገዳጅ አገር በቀል ተቋምና ማህበራዊ ስብስብ አለመኖሩ ሌላው ምክንያት ነው።

እነዚህ ከሞላ ጎደል ለጦርነቱ መራዘም ዋና ምክንያቶች ናቸው እንላለን።

ምንም እንኳን ጦርነቱን ለማቆም የሁለቱን አሸባሪ ሃይሎች ማለትም የወያኔንና የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽናን መሪዎችን ለማደራደር የውጭ አገር መንግሥታት ሳይቀሩ የተሰገሰጉበት የድርድር መድረክ በደቡብ አፍሪካ በፕሪቶሪያ ከተማ ውስጥ ቢጀመርም ውጤታማ ላለመሆኑ ብዙ ምልክቶች በመታዬት ላይ ናቸው።ድርድሩ አሁን የተጀመረ ቢመስልም ለረጅም ጊዜ ሲካሄድ የነበረና ውጤት አልባ ሆኖ እንደቀረ የአደባባይ ሚስጥር ነው።አሁንም ቢሆን በብዙሃኑ ዘንድ ይሳካል የሚል ግምት የለም።

ገና ድርድሩ ሳይጀመር የወያኔ ተደራዳሪዎች የሆኑት ጌታቸው እረዳ፣ወንድሙ አሳምነውና ተወልደ ገ/ስናይ የተባሉት በህመም ምክንያት ሆስፒታል መግባታቸውና የመጀመሪያው ቀን ድርድር መስተጓጎሉ ታውቋል።በሁለተኛውም ቀን ከሰዓት በኋላ መደረግ ባለበት ድርድር ላይ በተመሳሳይ ምክንያት ሳይገኙ ቀርተዋል።እዚህ ላይ ሊያሳዩ የሞከሩት በትግራይ ውስጥ የሕክምና ተቋማት በመውደማቸው ምክንያት ህክምና እንዳላገኙ ሆነው ችግሩን ለማሳዬት የሄዱበት ዘዴ ሲሆን፤ በደጋፊዎቻቸው ምክር የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡንና በተለይም የአፍሪካውያን አደራዳሪዎቹን ለማጃጃል የሠሩት አሻጥር ነው የሚል ግምት አለን።ግምታችን ከባዶ ሜዳ ላይ የታፈሰ አሉባልታ ሳይሆን የወያኔዎቹን ስነልቦና በሚገባ ለማወቅ በመቻላችን ነው።በዚህ አይነት አሻጥር የታጀበው ድርድር ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም።በድርድሩ ሂደትም ላይ የታዩት መንገጫገጮች የድርድሩን አለመሳካት አመላካቾች ናቸው።

የአብይ ውታፍ ነቃዮች በበኩላቸው ወያኔዎቹ ለድርድር የመውጣቱን አጋጣሚ ወደ አሜሪካና ካናዳ ለመሰደድ ሊጠቀሙበት ነው የሚል ወሬ ሲነዙ ተደምጧል።ይህንን በፊትም ቢሆን ትግራይ ውስጥ ተቀምጠው መሣሪያ ሲያመላልሱላቸው በነበረው የሱዳን አይሮፕላንም ሆነ በአሜሪካኖች ልዩ ምስጢራዊ በረራ ለማስፈጸም የሚያቅታቸው አልነበረም።ምናልባት የመጨረሻው ሊሆን ይችላል እንጂ አሜሪካኖችም ሆኑ አውሮፓውያን የወያኔ መሪዎች በከባቢው ባሉበት ሆነው ጥቅማቸውን የሚያስጠብቁላቸው እንዲሆኑ እንጂ ተሰደው ተወካይ አልባ መሆኑን የሚመርጡት አይመስልም። ከወያኔዎች ጋር ያቀራረባቸው ዋናው ነገር በቀጠናው ውስጥ የተላላኪ ሚና ተጫዋቾች ስለሆኑ ብቻ ነው።አብይ የነሱን ሚና የሚጫወትላቸው ከሆነ ወያኔዎቹን አፍንጫችሁን ላሱ የማይሉበት ምክንያት የለም።ለነሱ ቋሚ ጠላትና ቋሚ ወዳጅ የለም በሚለው መመሪያቸው ያንን ከማድረግ አይመለሱም።

ወያኔ የሚፈልገውን ካላገኘ ወይም ካልተሸነፈ በቀር አገር ሰላም ትሁን በሚል ፍላጎት ከአቋሙ ዝንፍ ይላል ማለት ዘበት ነው።አብይ አህመድም እንዲሁ ሥልጣኑን አምነው ከተቀበሉት የወያኔዎቹን ጥያቄ የማይቀበልበት ምክንያት አይኖርም።ለጦርነቱ ምክንያት የሆነው ይህ በመሆኑ ለጦርነቱም መቆም ምክንያቱ ይኸው ይሆናል።

አሁን ግን በአማራው ልዩሃይልና በፋኖ ተሳታፊነት  የመከላከያው ጦር ያገኘውን በላይነት ተከትሎ የወያኔ ጦር መቋቋም ተስኖት ብዙ ቦታዎችን እዬለቀቀ  እጁን የሚሰጠውና የሚሸሸው ቁጥሩ ብዙ እንደሆነ፣ ከዚያም አልፎ ተርፎ በሥልጣን ላይ የነበሩ በተለይም የባንክ ቤት  ኣላፊዎችና ሠራቶኞች እዬዘረፉ መሸሻቸውን ሰምተናል።ከነዚህም ኮረም ውስጥ የአንበሳ ባንክ ሃላፊ የነበረው ከሊለ አብርሃና እረዳቱ ደሳለኝ ድረስ የተባሉት 62 146 ብር፣6146 ዶላርና 190 ኤሮ ይዘው ሊጠፉ ሲሉ መያዛቸውን ሰምተናል።ቀደም ሲል ወያኔ ከመቀሌ ወጥቶ ወደ አራት ኪሎ ሲገሰግስ አበቃልን ብለው ካዝና ሰብረው፣ገንዘብ ሰርቀው ለመውጣት የሞከሩትን የአማራ ክልል ባለሥልጣኖች የነአገኘሁ ተሻገርን አሳፋሪ ድርጊት በነዚህም ላይ ለማዬት በቅተናል።አዎ የመጨረሻው ቀን ሲደርስ ሁሉም የዘረፈውን ዘርፎ እግሬ  አውጭኝ እንደሚል ከደርግ ባለሥልጣናት ጀምሮ ያዬነው ጉዳይ ነው።ለዚያም ነው በባለሥልጣኖቹ በውጭ አገራት የቤትና የንብረት ግዥው እሩጫ የተጧጧፈው።

ምንም እንኳን  አብይ አህመድ የሚያዘው ጦር ሃይል የበላይነቱን ይዟል ቢባልም  በምዕራባውያን በተለይም በአሜሪካኖቹ  የእቀባ  አርጩሜ  አስገዳጅነት ለሚፈልጉት ውጤት ተንበርካኪ የማይሆንበት ወኔ የለውም።ያሉትን ሁሉ ተቀብሎ ከማደር ወደኋላ አይልም። በኢትዮጵያ ኪሳራ በተለይም በአማራውና በአገር ወዳዱ ኢትዮጵያዊ መቃብር ላይ የራሱን ሥልጣንና የሚመራውን ድርጅት የኦነግ፣ኦሕዴድ ብልጽግና አገር የማፍረስ ዓላማ ከመተግበር  አይመለስም። ወልቃይትና ጠገሌ፣እራያና አዘቦ የመደራደሪያ ገጸ በረከቶች እንደሚሆኑ ባለፉት ጊዜያቶች ገልጸናል።አሁንም ቢሆን እነዚህ ለምና ሰፊ መሬቶች የድርድሩ መነሻና መድረሻ መሆናቸው እንደተጠበቀ ነው።እጣ ፈንታቸው በሕገ መንግሥቱ መሰረት በሚል ገመድ የተተበተበ ነው።ይህንን ወያኔዎቹም፣ደጋፊዎቻቸውም ኦነጋውያኑም የብልጽግና ጉጀሌዎች  የያዙትና የሚቀበሉት የጋራ አቋማቸው ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ላይ የመወሰን መብቱን ገፎ ያስገፈፈው የአብይ አህመድ አገዛዝ አሜሪካኖችና አውሮፓውያን ከዚያም ባለፈ አፍሪካውያን እንዲወስኑበት አሳልፎ መስጠቱ ምን ያህል ለአገራዊ ክብርና ልዑላዊነት ደንታ ቢስ መሆኑን ያሳያል።ድርድሩን ማዘጋጀትና መደገፍ ብቻ ሳይሆን አደራዳሪነቱና የውሳኔው ባለቤትነቱ ለነጮቹ ተላልፏል።አፍሪካውያን ለይምሰል  በፍለፊት ቁጭ ያሉ ከለላ ሆነዋል።ከዚህ የበለጠ ብሔራዊ ቅሌትና የእጅ አዙር ቅኝግዛትነት የለም። አብይ አህመድ ለይምሰል ኖሞር(No More) የሚል ጫጫታ በአደባባይ እንዲያሰሙ ደጋፊዎቹን አሰማርቶ በሌላ በር ለውጭ ሃያላን ታማኝነቱን ከመግለጽ አልተቆጠበም።ለካናዳው ጠ/ሚኒስትርም በስልክ ግንኙነቱ ወቅት ይህንኑ አረጋግጦለታል።ነጮቹ ያሉትን ያደርጋል፤የአገራችንን መሬትና የተፈጥሮ ሃብት ብቻም ሳይሆን ተቋማትንም እዬቸበቸበ የጠዬቁትን በመፈጸም  ታማኝነቱን ለማረጋገጥ ብዙ ሠርቷል።

የብልጽግና ተደራዳሪ  ቡድንና መሪው አብይ አህመድ  በድርድሩ ላይ ለይምሰል የአሜሪካኖችና አጃቢዎቿ ተጽእኖ ተቃዋሚ ለመምሰል ቢሞክርም የማታ ማታ ያሉትን ተቀብሎ፣የጠዬቁትን አስረክቦ ላለመመለሱ ዋስትና የለም።የነጮቹ ፍላጎትና ዓላማ በውድም በግድም የተላላኪያቸውን የወያኔን ሥልጣንና ቦታ ማስከበር፣ተንከባክቦ በመንበሩ ላይ እንዲቆይ ማድረግ  ነው።በነሱ መዳፍ ስር አልወድቅም ብሎ ያስቸገራቸውን ኢሳያስ አፈወርቂን ይነክስልናል፣ሌላውንም ያፍሪካ አገር እዬተላላከ

በቁጥጥራችን ሥር ያደርግልናል  ብለው የሚንከባከቡት ውሻ ተላላኪ ቡድን  እንዲሸሽ አይሹም። አቅሙ ቢዝልና የመኖር ህልውናው የሚያከትም ቢመስላቸው  የሱ ምትክ አስተማማኝ ተላላኪ መፍጠር አለባቸው።የመጀመሪያ ምርጫቸው በሥልጣን ላይ የተቀመጠው የአነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ሲሆን  ከዚያም በመቀጠል በሥልጣን ብቻ ከሚለዩት ተመሳሳይ ጸረ ኢትዮጵያ ከሆኑ የጎሳ ስብስቦች መሃል ሊሆን ይችላል።የነጁዋር ሞሃመድ ደፋ ደፋ ማለትም ለዚያ እጩነት የሚያበቃቸው ይሆናል። በጊዜያዊ  የሽግግር መንግሥት ስም  በአሜሪካኖቹ  የከባቢው የሰለላ ሳጥን ውስጥ  ተቀያሪ ጎማ ሆነው ተቀምጠዋል።በነዚህ የሚቋቋመው የሽግግር መንግሥት ሕዝቡና እኛ ከምንለው የሽግግር መንግሥት በብዙ መልኩ ይለያል።የነሱ የሽግግር መንግሥት ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አንድነት የሆኑት የጎሳ ስብስቦች የሚጠቀጠቁበት ሲሆን የሕዝቡና የእኛ የሽግግር መንግሥት ከዚያ የተለዬና ተቃራኒ ነው።የጎሳ ፖለቲካን ይጠዬፋል።በኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት ላይ አይደራደርም።

ስለድርድሩ ሂደትም ሆነ ዝርዝር  የተሰጠ ይፋዊ መግለጫ  የለም፤ሁሉም በሚስጥር እንዲይዘው ከማስጠንቀቂያ ጋር ስለተሰጠው ትንፍሽ አላለም።የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ላይ ባዳ ሆኖ  የማወቅ መብቱን ተገፎ የሚያቦኩት የውጭ ሃይሎች ሆነዋል።ሌላው ቀርቶ የአረቦችን ያህል እንኳን ቦታ አልተሰጠውም። የሰላም ምልክትና ጠበቃ የሆኑት የእምነት ተቋማት ድርሻ አላገኙም። በዚህ አይነቱ ከህደትና የውጭ አገሮች ደባ የሚደረስ ስምምነት ቢኖር ዕድሜው አጭር ነው። ሕዝቡን ያላካተተ ድርድር ለጊዜው  በሁለቱ አሸባሪዎች መካከል ስምምነት ቢደረስና ተኩስ ቢቆም  ጦርነቱ አበቃ ማለት አይደለም።ትልቁ ጦርነት ማለትም በሕዝቡና በተለይም የድርድሩ ሰለባ በሚሆነው የአማራ ማህበረሰብ ና  በሥልጣን ላይ ባለው አነግ፣ኦሕዴድ ብልጽግና  መካከል  አዲስ የጦርነት ምዕራፍ ሊከፈት የሚችልበት ዕድሉ ትልቅ ነው።አማራው ባርነትን እሺ ብሎ የሚቀበልበት ጊዜው ያከተመ ይመስላል።ችግሩ በቅጡ ተደራጅቶ መገኘቱ ላይ ነው፤ያም ቢሆን ካለፉት ውድቀቶቹ ተምሮ መልክ መያዙ አይቀርም የሚል እምነት አለን።

በድርድሩ ላይ ትኩረት የተሰጠው የተኩስ አቁም ስምምነት መድረሱ ላይ ሲሆን ፤በመቆሙ ላይ ሁለቱም ይስማማሉ፣ሆኖም ግን የዬራሳቸውን ቅድመ ሁኔታ አስቀምጠዋል።በወያኔዎቹ በኩል የመንግሥትና የኤርትራ ጦር ከትግራይ ይውጣ የሚለው ዋና ነጥብ ሲሆን፣ ተያይዞም የማንኛውም አገልግሎት መስከ ይከፈት ባዮች ናቸው።የብልጽግና ተደራዳሪዎች በበኩላቸው በቅድሚያ  የወያኔ ታጣቂ ትጥቁን ይፍታ ባዮች ናቸው።በመጨረሻ ሊሆን የሚችለው ቢኖር የትግራይ ሠራዊት የሚለው ስሙ እንደ ሌላው ክልል  በትግራይ ልዩ ሃይል በሚል መጠሪያ ተለውጦ ከማእከላዊው መንግሥት ጋር አብሮ የመሥራት  ስምምነት  እንዲቋጭ በአደራዳሪዎቹ በኩል ተቀባይነት ኖሮት ተግባራዊ ሳይሆን አይቀርም የሚለው ግምት የምንጋራው ይሆናል። በመጨረሻም መቀሌን ከበብኩ፣ማረኩ፣ወያኔ ተበታተነ የሚለው ጫጫታ  የወሬ ማሞቂያ ሆኖ ይቀርና እነደብረጽዮን የትግራይ ፈላጭ ቆራጭ፣ የአውሮፓውያን የተልእኮ አስፈጻሚ ሆነው ይቀመጣሉ።በቀጣዩ የወልቃይትና ጠገሌ፣የራያና አዘቦም መሬቶች በሕገመንግሥ መሠረት በሚለው ግርግር  ለወራሪው ህወሃት ተላልፈው  የሚሰጡበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።

የሁለቱ ስምምነት የሕዝቡ ስምምነት ማለት አይደለም።ለዘላቂ ሰላም እነዚህ ሁለት ጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖችና ያሰፈኑት የጎሳ ሥርዓት ተወግዶ በሕዝባዊና እውነተኛ ኢትዮጵያዊ በሆነ ሥርዓት መተካት አለበት።ያ እስኪሆን ድረስ የሕዝቡ ትግል ይቀጥላል።

ይህ በእንዲህ እያለ አብይ አህመድ ሕዝቡን ለማማለል ፣የውጭውንም ታዛቢ ለማወናበድ ኢትዮጵያ ከስንዴ ለማኝነት ወደ ላኪነት ተሻግራለ የሚል ፕሮፓጋንዳውን ይዞ ብቅ ብሏል።ኬንያና ጅቡቲም ለመግዛት ከተሰለፉት ብዙ አገራት መካከል ናቸው የሚል ወሬ ሲሰማ እውነት ቢሆን እኛንም ደስ ባለን ነበር፤ ግን በመሬት ላይ የሚታዬው እውነታ ከዚያ የራቀ ስለሆነ ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ብለን አልፈነዋል። ጉደኛው አብይ በዚህ ብቻ አልቆመም፣የብልጽግና የእድገት ጎዳናና የግሪን ሌጋሲን ውጤት ያዩ ሌሎቹ አገሮች ምነው ፈጣሪ ኢትዮጵያን ባደረገን እያሉ ነው በማለት ደረቅ ውሸቱን ለመንዛት ሞክሯል።በፈረደበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የጎሳ ፖለቲካ ጢብ ጢብ መጫወቱ ሳያንሰው በዚህ ቀውጢ ጊዜ ከመሰሎቹ ጋር ውድ ልብስ ለብሶ ኳስ ሲጫወት ማዬቱ ይበልጥ ንቀቱንና ግዴለሽነቱን አስመስክሯል።እዬሳቀ ኳስ በሚደበድብበት ሜዳ ላይ በተካሄደ የፎቶ ግርግር ቲማቲምና ድንች የሚሰበስበው አጥቶ ተበላሽቷል፤ምርት ሳይሆን ተጠቃሚ ጠፍቷል ሲል በርሃብ በሚሰቃዩት በሚሊዮን በሚቆጠሩት ዜጎች ላይ አላግጧል። በዚህና በሌሎቹ አድራጎቱ ጅል፣አለያም ያለበትን አገር የማያውቅ ማቶ ነው እንላለን።

ያሉበትን አገር የማያውቁት ብልጽግናዎች ብቻ አይደሉም፣የብልጽግናን ሥርዓትና ሕገ ጥፋት ተቀብለው በተቃዋሚ ስም የተደረደሩት እበላ ባዮችም ጭምር ናቸው።ትግላቸው ለሚያገኙት ትሩፋት እንጂ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም እንዳልሆነ ድምጻቸውን አጥፍተው መቀመጣቸው ማሳያ ነው። ሕዝብ ከኖረበት ቦታው ሲፈናቀል፣ጋዜጠኞች ሲታሰሩ፣ ፍርድ ሲዛባና ሲጣስ በቅርብ እርቀት ላይ ሆነው ድምጻቸውን ለማሰማት አልደፈሩም፤ይህም ዝምታቸው የወንጀሉ ተባባሪ ያደርጋቸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በድርድሩም ሆነ በውጭ ሃይሎች ተስፋ ማድረጉን ትቶ በራሱ ትግልና አንድነት ላይ መተማመን ብቻ የሚያዋጣው ይሆናል።በተለያዩ ጎራዎች የተሰለፈው አገር ወዳድ ወደ አንድነት ሰብሰብ ብሎ የተቀናጀ ትግል ካላደረገ ያገሩ ባለቤት መሆን ብቻ ሳይሆን የራሱንም ህይወት የመምራት ባለቤትነቱንም ያጣል። እንደ አሁኑም ብቻ ሳይሆን በባሰ ደረጃ የሚወስኑለት ሌሎች ይሆናሉ።

እውነተኛ ሰላም በሕዝቡ ተሳትፎና ፈቃድ እንጂ ጸረ ሰላም በሆኑት በህወሃትና በፈለፈላቸው የብልጽግና ጎሰኞች ስምምነት አይገኝም።

በአገሩ ጉዳይ ላይ ባለገሩ ሕዝብ ይወስን፣የውጭ ጣልቃ ገብነት ይቁም!